# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# የቤተመቅደስ መሪው ወደ ኢየሱስ መጣ


**ጸሐፊው**: Edward Hughes
**የተተረጎመው**: Eyerusalem Dechasa
**ምሣሌ አቅራቢው**: Byron Unger; Lazarus
**ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው)**: M. Maillot; Sarah S.



ታሪክ 41 ከ 60 ዎቹ መሃከል

**www.M1914.org**

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


**አማርኛ** Amharic

ኢየሱስ አንድ ቀን ወደ ቤተመቅደስ ሲሄድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቤት ሲያዋርዱ አገኘ። እነርሱም በቤተመቅደስ ውስጥ እንስሳትን እየሸጡ ገንዘብ ይለዋወጡ ነበር።



1

ከአውታርም ጅራፍ ሰራ። ኢየሱስም ነጋዴዎቹን ከቤተ መቅደስ አስወጣቸው። "እነዚህን ነገሮች ከዚህ አውጡ" ብሎም አዘዛቸው። ኢየሱስ የአባቱን ቤት ይወድ ነበርና "የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት" ብሎ ተቆጣ።



2



መሪዎቹ ኢየሱስ ቤተመቅደስን የማንፃት መብት እንዳለው ለማሳየት ምልክት እንዲያደርግላቸው ጠየቁ።

3



ኢየሱስም "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ውስጥ አነሳዋለሁ" ሲል መለሰላቸው። የማይቻል ነው! ቤተ መቅደሱን ለመገንባት አርባ ስድስት ዓመታት ፈጅቷል።

4

ኢየሱስ ግን የተናገረው ስለ ሰውነታቸው ነበረ። እንደ ቤተመቅደስ, ሰውነታችን የእግዚአብሔር መኖሪያ ስፍራ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ቢሞት እንኳን በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሞት እንደሚነሣው ያውቅ ነበር።



5



ምሽት ላይ ከቤተመቅደስ መሪዎች አንዱ ወደ ኢየሱስ መጣ። ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን በተዓምራቶቹ ያውቃል። ኒቆዲሞስ ስለ እግዚአብሔር የበለጠ ለመማር ወደ ኢየሱስ መጣ።

6



ኢየሱስ ኒቆዲሞስ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ዳግመኛ መወለድ እንደሚያስፈልጋቸው ነገረው። ኒቆዲሞስ ግን አልተረዳውም ነበር። አንድ ትልቅ ሰው እንደገና እንደ ሕፃን እንዴት ሊወለድ ይችላል? ከዚህም በላይ ሃይማኖተኛ ነበር። ይህ በቂ አልነበረም ማለት ነው?

7



ኢየሱስ "ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው" ሲል አስረዳ። "የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ነፋስ ነው። ሰዎች ነፋስን አያዩም ወይም አያስተውሉም። ነገር ግን ሲነፍስ ብቻ ያዩታል።"

8


ኢየሱስም ከረጅም ጊዜያት በፊት የእስራኤላውያን ልጆች በሙሴ ላይ ሲያማርሩ እንደነበር ለኒቆዲሞስ አስታወሰው። "ምግብ የለንም፣ ውኃም የለምእግዚአብሔር የሚሰጠንንም ዳቦ አንፈልግም" ብለው ጮኹ።
9
የሕዝቡ ኃጢአት እግዚአብሔርን አስቆጣው። በመካከላቸውም እሳት የሚተፋ እባብ ላከባቸው። እባቦቹ ሰዎቹን ነደፏ ቸው ብዙዎችም ሞቱ።
10
ህዝቡም "ኃጢአትን ሠርተናል እነዚህን እባቦች እንዲያጠፋልን ወደ እግዚአብሔር ፀልይ።" ብለው ሙሴን ለመኑት። ስለዚህ ሙሴ ለእነሱ ጸለየላቸው። እግዚአብሔር ግን እባቦችን አላጠፋቸውም ነበር።
11
እግዚአብሔርም ሙሴን እሳትን የሚተፋ እባብ እንዲሠራና በእንጨት ላይ እንዲሰቅለው ነገረው። "በእባቦቹ የተነከሰ ሁሉም ሰው የተሰቀለውን እባብ ባየ ጊዜ በሕይወት ይኖራል" በማለት ቃል ገባላቸው። ሙሴ የናስ እባብ ሠራ እናም እባቡ የተመለከቱ ሰዎች ተፈወሱ።
12
ኢየሱስም ኒቆዲሞስን, የሰው ልጅ እንደ ናስ እባብ ከፍ ከፍ እንዲል እንዳዘዘው ነገረው። ኢየሱስ ለኃጢአተኞች ስለሚሞትበት ስለ መስቀል መናገሩ ነበር።
13
ኢየሱስም አለ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"
14













የቤተመቅደስ መሪው ወደ ኢየሱስ መጣ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዮሐንስ 2-3, ዘሑልቁ 21

"የቃልህ ፍቺ ያበራል."
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16